አንድ ሙስሊም ‐ወይም ሙእሚን‐ የአላህ ባሪያ ውዱእ በሚያደርግበት ጊዜ ፊቱን ሲያጥብ በዓይኑ የተመለከተው ኃጢአት ሁሉ ከፊቱ ከውሀው ጋር አብሮ ይፀዳለታል። - ወይም ከመጨረሻው የውሃ ጠብታ ጋር አብሮ ይራገፍለታል።

ከአቡ ሁረይራ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) እንዲህ ብለዋል፦ "አንድ ሙስሊም ‐ወይም ሙእሚን‐ የአላህ ባሪያ ውዱእ በሚያደርግበት ጊዜ ፊቱን ሲያጥብ በዓይኑ የተመለከተው ኃጢአት ሁሉ ከፊቱ ከውሀው ጋር አብሮ ይፀዳለታል። - ወይም ከመጨረሻው የውሃ ጠብታ ጋር አብሮ ይራገፍለታል። - እጁን ሲታጠብም እንዲሁ እጆቹ እየዳሰሰች የፈፀመችው ኃጢአት ሁሉ ከውሀው ጋር አብሮ ይፀዳለታል። - ወይም ከመጨረሻው የውሃ ጠብታ
ጋር አብሮ ይራገፍለታል። - እግሩን ሲታጠብም እንዲሁ እግሮቹ ስትራመድ የፈፀመችው ሀጢአት ሁሉ ከውሀው ጋር አብሮ ይፀዳለታል። -
ወይም ከመጨረሻው የውሃ ጠብታ ጋር አብሮ ይራገፍለታል። - ልክ እንደዚሁ እያለ ከኃጢአት ንጹሕ ሆኖ ከዉዱኡ እስኪወጣ ድረስ ከኃጢአቱ ይፀዳል።"
[ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) አንድ ሙስሊም ወይም ሙእሚን ዉዱእ ያደረገ ጊዜ በዉዱእ ሂደት ፊቱን ሲታጠብ በአይኖቹ የተመለከታቸው ትናንሽ ወንጀሎች ሁሉ ከታጠበ በኋላ ከሚወርደው ውሃ ጋር ወይም ከመጨረሻው የውሃ ጠብታ ጋር ከፊቱ እንደሚራገፍ ገለፁ። እጆቹን የታጠበ ጊዜ ደግሞ እጆቹ የሰራቻቸው ሁሉም ትናንሽ ወንጀሎች ከውሃው ጋር ወይም ከመጨረሻው የውሃ ጠብታ ጋር ከእጁ እንደሚራገፍ ገለፁ። ሁለቱን እግሮቹ የታጠበ ጊዜ ደግሞ እግሮቹ የተራመደችባቸው ሁሉም ትናንሽ ወንጀሎች ከውሃው ጋር ወይም ከመጨረሻው የውሃ ጠብታ ጋር ከእግሩ እንደሚራገፍ ገለፁ። ይህም ውዱኡን ሲያጠናቅቅ ከትናንሽ ወንጀሎቹ ፀድቶ እስኪወጣ ድረስ ነው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3284